በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

# ተዋሕዶ

## በፋሲል ኪዳኔ

### ❖ የዚህ አጭር መንፈሳዊ ተውኔት መሰረታዊ አላማ፡-

❖ ተዋሕዶ እምነታችን ሳይገባቸና ሳይገባን ዘለን ወደ ደጇ በገባን አገልጋዮች ምክንያት ምን እንደመሰለች ለማሳየትና ነቢዩ ኤርሚያስም *‹‹በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሷም ላይ ሒዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ .....››* በማለት እንደተናገረው ትክክለኛው የክርስትና ጎዳና የትኛው እንደሆነ በውስጥም በውጪም ላሉ ክርስትያኖች ለመግለፅ እና በዚህ በቀድሞውና በጥንቱ መንገድ ብቻ እንዲጓዙ ለማስቻል ነው፡፡

❖ *‹‹እነርሱ ግን አንሔድባትም አሉ›› ኤር.6፡16*

❖ **ይህ መንፈሳዊ ተውኔት የሚያጠነጥነው በቤተ-ክርስትያን ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሲሆን የሚሰራውም በሰባት ሰዎች ነው፡፡**

❖ **መሠረት እና ዳንኤል** እህትና ወንድም ሲሆኑ ዳንኤል ዘማሪ ነው፡፡ መሠረት ደግሞ ምንም በአገልግሎት ሕይወት ውስጥ ባትኖርም ጠንክር የለ የክርስትና እምነት ያላት መንፈሳዊት ሴት ናት፡፡

❖ **ፍሬዘር፡-** መምህር ሲሆን ከነመሰረት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው የቤ/ክ አገልጋይ ነው፡፡

❖ **ምሕረት፡-** ሰንበት ተማሪ ስትሆን የመሰረት የቅርብ ጓደኛ እና የዳንኤል ደግሞ ፍቅረኛ ናት፡፡ የምትወክለውም ገፀ-ባሕርይ ግዴለሽ አገልጋይ ሆና ነው፡፡

✓ */ተውኔቱ ሲጀምር ተዋሕዶን ወክላ የምትሰራው ሴት ነጭ የሃገር ባህል ልብስና ካባ አድርጋ አክሊል ደፍታ መድረክ መሃል ላይ ቁጭ ብላ ትታያለች፡፡ መሠረትና ዳንኤልም አጠገብ ሳጠገብ ቁጭ ብለው በአንድ ጉዳይ እየተከራከሩ እንመለከታቸዋለን/*

❖ ***መሠረት፡-*** መምህሩን ፈርተው እግዚአብሔርን የማይፈሩ ዘማሪውን ወደው እግዚአብሔርን የማይወዱ ክርስትያኖች ከእለት ወደ እለት እየበዙና እየተባዙ እየመጡ ነው

❖ **ዳንኤል፡-** ታዲያ ምን ያስደንቃል አንድ ቀን ይወዱት ይሆናል

❖ ***መሠረት፡-*** ምን ማለት ነው?

❖ **ዳንኤል፡-** አገልጋዩን የወደዱበት ፍቅራቸው ሲያልቅ .... ማለቴ ነው

❖ **መሠረት፡-** ይሔ እንዴት ሊሆን ይችላል ….

❖ **ዳንኤል፡-** የዘመኑ ክርስትና ልክ እንደ እግርኳስ ጨዋታ በድጋፍ ስለሆነ ብዙ የሚያሳስበኝ ነገር አይደለም

❖ **መሠረት፡-** እንዲያውም ሳስበው ለህዝቡ መጥፋት ተጠያቂዎቹ እናንተ አገልጋይ ነን ብላችሁ በቤቱ የተሰባሰባችሁት ይመስለኛል

❖ **ዳንኤል፡-** ጫን ያለው መጣ የጠፋውን ህዝብ ሰበሰብን ስንል … ጭራሽ እኛ ሆንን ተጠያቂዎቹ

❖ **መሠረት፡-** ምዕመኑ ድንፅ ማጉያውን ሳይሆን ባለድምፁን ጌታ ብቻ እንዲመለከቱ ምን አደረጋችሁ … ሌላውን ተወው አንተ እራስህ እንደዘማሪነትህ ምን አደረክ?

❖ **ዳንኤል፡-** ማን እኔ?

❖ **መሠረት፡-** አዎን አንተ

❖ **ዳንኤል፡-** ምን ያላደረኩት ነገር አለ

❖ **መሠረት፡-** ለምሳሌ…..

❖ **ዳንኤል፡-** ለምሰሳሌ …. ለምሳሌ …. እ… የትኛውን ጠርቼ የትኛውን ልተወው በሰራዋቸው የዝማሬ ካሴቶች ውስጥ ሁሉም ማለት እችላለው ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያጣጥሙ አስቤ ነው የሰራሁት

❖ **መሠረት፡-** ማን አንተ?

❖ **ዳንኤል፡-** አዎን እኔ ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?

❖ **መሠረት፡-** አይ ምንም … ብቻ የሆነ ነገር ገርሞኝ ነው … ጥሩ ተናግርሃል እንደ እህትነቴ እስከማውቀው ድረስ ግጥምና ዜማ ስትሰራ አይቼህ አላውቅም እስከዛሬ የሰራኸውም ቢሆን ድምፅ ስላለህ ሰዎች ሰጥተውህ ነው በዚህ ምንም አይነት ተቋውሞ የለኝም ግን የምትዘምራቸው ዝማሬዎች ምን ያህል ከሕይወትህ ጋር የተቆራኙ ናቸው? አሁን አሁን እየወጡ ያሉ ዝማሬዎች የወደቀውን ለማንሳት የታመመውን ለመፈወስ ያዘነውን ለማፅናናት ጉልበት ያነሳቸው እየሆኑ ነው ለምን? ከዚህም ጋር ተያይዞ ደግሞ ከያሬዳዊ ዜማ የወጡ የዘፈን መለወጫ ሆነዋል

❖ **ዳንኤል፡-** ይሔ እኔን አይመለከተኝም … እኔን የሚመለከተኝ በመዘመሬ የሚከፈለኝንና የማገኘውን ገንዘብ ብቻ ነው፡፡ ያሬዳዊ ዜማ ሆነ አልሆነ ለእኔ ትርጉም የለውም

❖ **መሠረት፡-** አላማህ ይሔ ነው?

❖ **ዳንኤል፡-** አዎን

❖ **መሰረት፡-** ታዲያ እንደኛኽን ለምን ወደ ዘፈን አለም አትገባም

❖ **ዳንኤል፡-** ዘፈን ኃጢአት ነው

- ***መሠረት፦*** አሁን እያደረክ ያለኸው ፅድቅ  መሆኑ  ነው

- ***ዳንኤል፦*** በእርግጠኝነት አዎን

- ***መሠረት፦*** አትሳሳት ከሁሉ  በላይ  የባሰው  ግፍና   ኃጢአትስ  ክርስትናን  ተገን  አድርጎ ለግል ጥቅም የሚደረገው መሯሯጥ  ነው፡፡ እነዚያስ አንዴ  በግልፅ   በአደባባይ   ወጥተው ይዘፍናሉ አንድ ቀን ጌታ ልቦና  የሰጣቸው እለት ይመለሱ  ይሆናል  ከዚህ ይልቅ   ግን ለቤተ-ክርስትያን  ትልቅ  አደጋ የሆነባት በስሯ ተጠልለው የራሳቸውን የግል  ጥቅም በሚሟላት ስርዓቷን በድፍረት በመሻር በሚመላለሱ አገልጋይ ናቸው በምትባሉት ግን የበግ ለምዱን  ብቻ በለበሳችሁት  በእናንተ  ምክንያት ነው

- ***ዳንኤል፦*** ያኔ በዚያን ዘመን የነበሩት እንደነበራቸው  አመለካከትና  ስልጣኔ  ማድረግ የሚገባቸውን አዘደረጉ በቃ አድርገው አፈፉ ዛሬ ላይ ሆነን እነሱ በተጓዙበት  አካሔድ  እንሒድ ማለት  ቀልድ ይመስለኛል ስለዚህ በግልፅ ልነግርሽ የምችለው ቤተ-ክርስትያን አካሔዷና  ስርዓቷ በአዲስ  መልክ መቀየርና መታደስ አለበት

- ***መሰረት፦*** ምን ጭራሽ …….

- ***/ፍሬዘርና ምሕረት ይገባሉ/***

- ***ምሕረት፦*** ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን

- ***መሠረት፦*** ሰላማችሁ ይብዛልን እንደምን ዋላችሁ ***/ሰላም ይባባላሉ/***

- ***ፍሬዘር፦*** ***/የዳንኤልን ፊት ትኩር ብሎ እየተመለከተ/*** ባልሳሳት  በሆነ ጉዳይ እየተከራከራችሁ ነበር ልበል?

- ***መሠረት፦*** አዎን በተዋሕዶ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ እየተነጋገር ነበር

- ***ምህረት፦*** ተዋሕዶ ምን ሆነች?

- ***መሠረት፦*** የወላድ መካን ሆናለች

- ***ፍሬዘር፦*** እንዴት?

- ***መሠረት፦*** ታማኝ በመንገዷ የሚጓዙ አገልጋዮች ስላጣች

- ***ምሕረት፦*** ስለምንድነው የምታወሪው  ከበረቱ  የጠፉትን   መንጎች  ወደ   በረቱ  እየመለሱ ያሉ  በዝማሬውም ምድርን ለመክደን  ብዙ የሚደክሙ አገልጋዮች  በበዙበት   ዘመን   የወላድ መካን  ሆናለች  ማለት  ለእኔ አይዋጥልኝም .. አትሳሳቺ መሲ ለቤ/ክርስትያን የስኬት እና ወርቃማ ዘመን አሁን ይመስለኛል

- ***መሠረት፦***  ወርቃማው  ዘመን  አልሺው  ለተዋሕዶስ  የስኬትና   ወርቃማው   ዘመን የነበረው  አራተኛው  መቶ ክ/ዘመን ነበር ለዚች ቅድስት ቤተ-ክርስትያን ራሳቸውን   አሳልፈው የሰጡ  እነ ቅዱስ አትናቲዎስ፣ እነ ቅዱስ ኤፍሬም ፣  እነ ቅዱስ  ዲዮስቆሮስ  ሌሎችም  አባቶች የተነሱበት ዘመንን  ነው  ወርቃማ  ዘመኔ   ብላ የምታከብረው ሰንበት ተማሪ አይደለሽ ሒጂና የቤ/ክርስትያን  በአለም  መድረክ ያሳለፈችውን ሒደት  ተማሪ ወርቃማውን ዘመን ታገኚዋለሽ ***/በጣም ትናደዳለች/***

- ***ምሕረት*፡-** ስንምድነው የምታወራው?
- ***ዳንኤል*፡-** እኔ ምን አውቄ እሷን ጠይቂአት
- ***ምሕረት*፡-** ወይኔ ጉዴ አሞሻል እንዴ?
- ***መሠረት*፡-** አላመመኝም ጤነኛ ነኝ የታመማችሁትስ እናንተ ናችሁ
- **ፍሬዘር፡-** እኛን ነው
- ***መሰረት*፡-** አዎን እናንተን
- **ፍሬዘር፡-** የባሰ አታምጣ አለ ዘማሪው
- **ፍሬዘር፡-** **/በ*ፌዝ*/** እሺ ሲስተር መሰረት የህክምና ውጤታችን ምን በሽታ እንዳለብን ያስረዳል

❖ ዳንኤልና ምሕረት በአነጋገሩ ተገርመው የፌዝ ሳቅ ይስቃሉ

- **ፍሬዘር፡-** ***/ስልኩ ይጮኻል/*** ሔለው….. አቤት ….. ስምረት እንዴት ነሽ ….. እግዚአብሔር ይመስገን ….. ምን እንሆናለን ብለሽ ነው …. ስራ ምን አይል….. ያው አንዱ ደብር ሲያባርሩን ሌላ ደብር ሔደን እንሰራለን ….. አይደል ***/ይስቃል/*** እሺ ለማንኛውም በኋላ እደውልልሻለው እንገናኛለን …. በአጋጣሚ ሁሉም አጠገቤ ናቸው …. እሺ … እልልሻለው …. እሺ … እሺ … ቻው ስምረት ናት ሰላም ብላችኋለች ጨረሳችሁት ልበል?
- ***መሠረት*፡-** ምኑን?
- **ፍሬዘር፡-** ክርክራችሁን
- ***መሠረት*፡-** አንተ እየጠበቅንህ ስለነበር አልጨረስንም
- **ፍሬዘር፡-** ለምንድነው እኔን የምትጠብቁኝ?
- ***መሠረት*፡-** ከክርክሩ አካል ውስጥ አንዱ አንተ ስለሆንክ
- **ፍሬዘር፡-** ምን?
- ***ዳንኤልን ምሕረት* አንድ ላይ/** ወደ እሱ ዞርሽ ደግሞ?
- ***መሠረት*፡-** መዞር አይደለም ይሔ ጉዳይ ሁላችንንም ስለሚመለከት ነው
- ***ዳንኤል*፡-** እንዴት?
- ***መሠረት*፡-** ምን እንዴት ትላለህ ተዋሕዶ የንግድ ቤት ሆናለች እኮ
- ***ምሕረት*፡-** እውነት አንቺ ልጅ በትክክል አሞሻል ለምን ሃኪም ቤት አትሔጂም
- ***መሠረት*፡-** እርግጥ ሕመሜ አንቺ እንደምታስቢው የሥጋ ሳይሆን የመንፈስ ነው ቅዱስ ዳዊት ‹‹የቤትህ ቅናት በላኝ›› አይደል ያለው ቆይ አንተ መምህር አንቺ ደግሞ ሰንበት ተማሪ አንተኛው ደግሞ ዘማሪ ነኝ ነው ያልከው?

- **ዳንኤል፡-** ምነው ተጠራጠርሽ እንዴ?

- **መሠረት፡-** ኧረ በጭራሽ

- **ምሕረት፡-** አሁን እሱን ተሁትና ምን ለማለት ፈልገሽ ነው ፍሬዘርን አስተማሪ ዳኒን ደጎሞ ዘማሪ እኔን ሰንበት ተማሪ ያልሽው?

- **መሠረት፡-** ስለሆናችሁ

- **ሶስቱም አንድ ላይ፡-** ብንሆንስ?

- **መሠረት፡-** ጉዳዩ ከእኔ ይልቅ በይበልጥ እናንተን ይመለከታል

- **ዳንኤል፡-** የትኛው ጉዳይ?

- **መሠረት፡-** አሁን እየተነጋገርንበት ያለው ጉዳይ

- **ምሕረት፡-** አልገባኝም?

- **መሠረት፡-** አሁን አሁን በቤተክርስትያን አከባቢ እየተጸፈፀመ ስላው አንገብጋቢ ጉዳይ ማለቴ ነው

- **ፍሬዘር፡-** ይሔ እኮ ከእኛ አቅም በላይ ነው መሰረት

- **መሠረት፡-** አይደለም

- **ዳንኤል፡-** ቆይ አንድ ሰው ለመኖር ገንዘብ ያስፈልገዋል አይደል

- **ምሕረት፡-** ትክክል

- **ዳንኤል፡-** ታዲያ ምንድነው የሚያስደነግጠን የእግዚአብሔርን ቤት የንግድ ቤት አደረጋችሁት .... ገለመሌ የሚል ቋንቋ እኔ አይገባኝም መምህሩስ አስተማረ ገንዘብ አገኘ ዘማሪውም ዘመረ የዘመረበትን የድካሙን ዋጋ አገኘ በቃ አለቀ

- **ፍሬዘር፡-** /በቁጣ/ ዳንኤል እንደዚማ አትበል

- **ዳንኤል፡-** ለምን እውነቱን ስለተናገርኩ

- **ፍሬዘር፡-** እርግጥ እውነት ይነገር ከተባለማ በዘማሪያን ላይ የሚታይ አንዳንድ ፈር የለቀቁ ችግሮች እንዳሉ አውቃለው

- **ዳንኤል፡-** የራሳችሁን ሳታስተካክሉ የሌላውን ስህተት ለማውራት እንዴት ፈጠናችሁ ባክህ

- **ፍሬዘር፡-** አልገባኝም ምን ለማለት ፈልገህ ነው

- **ዳንኤል፡-** እውነቱን ልንገርህ ስህተት ያለው እኛ ዘማሪያን ጋር ሳይሆን እናንተ አስተማሪ ነን በምትሉት እና ሰንበት ተማሪዎች ላይ ነው ተጠያቂዎቹ እናንተ ናችሁ

- **ምሕረት፡-** ከአንተም ብሶ አፍህን ሞልተህ ሰንበት ተማሪዎች ስትል ትንሽ አታፍርም ምን አደረገን በአውደ ምህረት ለሚፈጠረው ችግር መንስኤው እናንተ አይደላችሁም እንዴ?

- **ፍሬዘር፡-** ነገርን ነገር ያነሳዋል ነው የተባለው በዝማሬ ሰዓት በከበሮ እና በአንድንድ ጥቃቅን ነገሮች የምትጣሉት ለብዙዎች መጥፋት ምክንያቶቹ እናንተ ናችሁ

- **ዳንኤል፡-** የራሳችሁን ስህተት ለመሸፋፈን ነው?

- **ፍሬዘር፡-** ለመሸፋፈን

- **ዳንኤል፡-** አዎን ለመሸፋፈን መድረክ ላይ እና ከመድረክ ጀርባ ያለው ሕይወታችሁ አሁን አሁንማ ለሁሉም በግልፅ እየታወቀ ነው፡፡ ጹሙ ትላላችሁ እናንተ ግን አትፆሙም ስለዘፈን ብዙ ትናገራላችሁ ከዘፈን ሕይወትን ግን ገና አልተላቀቃችሁም አሕያ ቀምሳ የማታውቀውን ማር ብዙ ጊዜ ከገጠር ወደ ከተማ እንዳመላለሰች እናንተም ያልኖራችሁበትንና ለመኖርም ያላሰባችሁበትን ቃል ስትናገሩ ይሔው እስከዛሬ አላችሁ እርስ በርሳችሁ አትስማሙም ወንጌልን መስበክ ትታችሁ አንዱ አንዱን መንቀፍ ሆኖ አይደል እንዴ ስራችሁ

- **ፍሬዘር፡-** ይሔ እኔን አይመለከተኝም የሚመለከታቸውን ሒድና ለእነሱ ንገራቸው

- **ዳንኤል፡-** እንዴት አይመለከተኝም ትላለህ እስኪ ንገረኝ አንተ አገልጋይ ነህ ወይስ ሰራተኛ?

- **ፍሬዘር፡-** አገልጋይ

- **ዳንኤል፡-** ለምን ታዲያ ወላዋይ ትሆናለህ ቅድም በስልክ ስራ ስራ ስትል አልነበር ታዲያ አሁን ቃልህ ለምን ተቀየረ?

- **መሠረት፡-** በቃችሁ እንደዚህ ተከፋፍላችሁ ነው እግዚአብሔርን የምታገለግሉት የተዋሕዶ ጠበቆች የቀደሙት አባቶች ስለዚች ቅደስት ሃይማኖት ሕያው ነፍሳቸውን አሳልፈው ሰጡ አንተስ አንቺስ እኛስ ምንድ ነው ዋጋ የከፈልነው ዛሬ ስርአቷ ትውፊቷ ጊዜ ያለፈበት ስለሆነ መታደስ አለበት የሚሉ የጉያ ውስጥ እሳት ሆነው ሊያቃጥሏት በተነሱበት ሰዓት እውን ምን አደረግን እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ ብቻ እያመለክነው እና እያገለገልነው ይሆን ወይስ እኛም ለቤተክርስትያን ተጨማሪ የእግር እሳት እየሆን ይሆን?

- **ዳንኤል፡-** እንዴት ተደርጎ እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ ብቻ የሚመለከው

- **መሠረት፡-** የምትዘምረው ድምፅ ስላከህ ገንዘብ ለማግኘት ከሆነ ተሳስተሃል እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ ብቻ ተከተለው ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው ይጨመርልሃል አላማህን አስተካክል አንቺም ሰንበት ተማሪዋ እህቴ ብዙ የቤት ስራ አለብሽ ከዘማሪዎች ጋር በሚፈጠር አንዳንድ አለመግባባት መድረክ ላይ መጣላት እግዚአብሔር የሚከብርብት የጀብድ ስራ ነው ብለሽ የምታስቢ ከሆነ ተሳስተሻል ከዚህ ይልቅ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ለሚፈልጉ ክርስትያኖች መሰናክል መሆን ነው እርግጥ እኛም ቁጭ ብለን በምንገለገለው ምዕመናን ላይም ችግር አለ የምስማው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ክርስቶስ የተናገረውን ሳይሆን ከመስቀሉ ስር ያሉትን የሰቃዮቹን አሉባልታ ወሬ ነው፡፡ የምንመለከተውም መስቀሉንና የተሰቀለውን ሳይሆን ምድራዊ የሆኑ ሰዎችን ነው፡፡ እናንተም ስለ እኛ ያላችሁ አመለካከት ትክክል ነው ብዬ አላምንም ቁጭ ብለው ቃሉን የሚማሩ ክርስትያኖች ምንም የሚያውቁ አይመስላችሁም ይሔ ግን ስህተት እንደሆነ ዛሬ ተረዱ ከቃል ይልቅ በሕይወት ስበኩን አስተምሩን እንደ እናንተ የጠለቀ እውቀት ባይኖረኝም ስለ

ሃይማኖቴ ግን ማወቅ ያለብኝን እውቃለው በዚህም ደስተኛ ነኝ። ለመጨረሻ ጊዜ ትሰሙኝ ከሆነ አንድ ነገር ብቻ ልንገራችሁ ለዚች ቅድስት ቅድስት ቤተ-ክርስትያን የሚጠቅማት እርስ በርሳችን ተለያይተን እየተካሰስን መኖራችን ሳይሆን አንዳችን የአንዳችንን ሸክም እየተሸከምን በፍቅር መኖራችን ነው። በትክክለኛው የክርስትና ጎዳና ለመጓዝ የሚፈልግ ካለ ከእሱ ጋር ህብረት አደርጋለው ከዚህ ውጪ ግን ከሚኖር ሰው ጋር ከዚች ሰዓት ጀምሮ አንድነትም ህብረትም የለኝም። መጣው ውሳኔአችሁን ታሳውቁኛላችሁ */ወደ ውስጥ ትገባለች/*

- **ፍሬዘር፦** እያደር ጉድ ይሰማል አሉ ይሔ ከእኔ አቅም በላይ ነው ልወጣው አልችልም ስለዚህ የማልችለውን ነገር እንኳን ለመስራት ለሙከራ አልነሳም እራሱ ባለቤቱ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነውና የፈቀደውን ያድርግ */ከመቀመጫው ተነስቶ ሊሔድ ሲል/*
- ምሕረት፦ ወዴት ልትሔድ ነው?
- ፍሬዘር፦ ቀጠሮ አለብኝ ደሕና ዋሉ */ይሔዳል/*
- **ዳንኤል፦** አንቺስ ምን ወሰንሽ?
- **ምሕረት፦** ምንም
- **ዳንኤል፦** ከዚህ በኋላ እዚህ ቤት መኖር አልፈልግም ቤት ተከራይቼ የራሴን ኑሮ እኖራለው ከዚህ በኋላ አብረን በፍቅር መቀጠል የምንችለው የእኔን ጎዳና ስትከተሒ ብቻ ነው አንቺም እንደዚያች ወግ የምታጠብቂ ከሆነ የምርጫሽ ነው አብረን እንድንኖር ከፈለግሽ ተከተሒኝ ቤት ወጥተን እንፈልግ */ወጥቶ ይሔዳል/*
- **ምሕረት፦** */ባለችበት ቁጭ ብላ ታመነታለች በመጨረሻም ተነሰታ/* ዳኒ ዳኒ …. እሺ ጠብቀኝ */ተከትላው ወጥታ ትሔዳለች/*
  - **/ተዋሕዶን ወክላ የምትሰራው ሴት ከፊት ይልቅ ፊቷ በሃዘን ተውጦ እንመለከታለን/**
- **ተዋሕዶ፦** */በሲቃ/* እሺ ማን ይከተለኝ ማንስ ቃሌን ይስማ ማን ይታዘዝልኝ ያኔ አሕዛብና ነገስታት ሁሉ ጠሉኝ አሳደዱኝ በብዙ ጭንቅና መከራ ውስጥ አልፌ ይሔው ለዚህ ክብር በቃው ዛሬ ደግሞ የገዛ ከማሕፀኔ የወጡ የወለድኳቸው ልጆቼ ሸሹኝ አመፁብኝ እራቁኝ ማን ያፅናናኝ ማን ከመከራዬ ይካፈል */ታለቅሳለች/*
- **ቅዱስ አትናቴዎስ፦** */ከበስተቀኝ ይወጣል ሔዶ እግሯ ስር ወድቆ/* እ ናቴ ተዋሕዶ ሃዘንሽ እረፍት ነሳኝ ይሔው ከመቃብር አስነስቶ አስመጣኝ ስለምንድ ነው የምታዝኚው? ስለምንስ ነው የምታለቅሺው?
- **ተዋሕዶ፦** የወላድ መካን አድርገው ጥለውኝ ስለሔዱት ልጆቼ ከማሕፀኔ ወጥተው ጡቶቼን ጠብተው ያሳደኳቸው ልጆቼ ጠሉኝ ብቸኛ አደረጉኝ ልጄ አትናቴዎስ ቃሌን የሚሰማኝ በመንገዴም የሚጓዝ ሰው አጣው ሁሉም በራሱ ሃሳብና ፍላጎት የሚቅበዘበዝ ሆነ ማን እሺ ብሎ ይታዘዝልኝ ማነው እኔ አለውልሽ ብሎ መከራዬን የሚቀበለው

- **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡-** */ከበስተ ግራ ይወጣና እግሯ ስር ወድቆ/* እማማ ተዋሕዶ ጭንቀትሽ ዋይታሽ አላስችል ቢለኝ ላስጽናናሽ አይዞሽ ልልሽ ይሔው ወደ አንቺ መጣው አይዞሽ እናቴ ተዋሕዶ አትዘኚ

- **ተዋሕዶ፡-** ስለምን አልዘን ልጄ ዮሐንስ አፈወርቅ ስርዓቴን አፈረሱት አርጅተሻልና እናድስሽ አሉኝ አስተምሬ ተንከባክቤ ያሳደኳቸው እናስተምርሽ አሉኝ ታዲያ እንዴት አልዘን በቅጥሬ ውስጥ አፍኒንና ፊኒያንስ የእርኩሰትን ስራ ፈፀሙ ምን አለበት በሚል ድፍረት የማይገባን ነገር አደረጉ ቅጥሬን እንዲጠብቅ አደራ ያልኩትም አገልጋዬ ኤሊም ዝምታን መረጠ

- **ቅዱስ አትናቴዎስ፡-** አይዞሽ እናቴ ተዋሕዶ ሁሉም የራሱን ጎዳና የመረጠው ያልገባውና ሊደርስበት ያልቻለው እውነት ስላለ ነው

- **ቅዱስ ዮሐንስ አፈርቅ፡-** አዎን አንድ ቀን የተከፈለላቸው ዋጋ ሲገባቸው እና ሲያስተውሉ ይቅር በይን እያሉ ወደ አንቺ ይመጣሉ ወደ እግርሽም ይወድቃሉ እናቴ ተዋሕዶ አንድ ቀን አዎን አንድ ቀን የእግርሽንም ትንቢያ ይልሳሉ

- *ተዋሕዶ፡- /ቅዱስ አትናቴዎስንና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እቅፍ አድርጋ ታለቅሳለች/*

- *ቅዱስ አትናቴዎስና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግራና ቀኝ ይዘዋት ይወጣሉ፡፡*

- *መሰረት፡- /ከውስጥ ትወጣለች ሁሉም ጥለዋት በመሔዳቸው ቁጭ ብላ ታዝናለች ፍጹም ይገባል ቤቱን በአትኩሮት ይመለከታል/*

- **ፍፁም፡-** *ሠላም ለዚህ ቤት ይሁን እንደምን ዋልሽ መሲ*

- ***መሠረት፡-*** እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ዋልክ ፍጼ */ሠላም ይባባላሉ/*

- **ፍፁም፡-** *ምን ሆነሻል በጣም ተከፍተሻል የተፈጠረ ችግር አለ*

- ***መሠረት፡-*** *አዎን*

- **ፍፁም፡-** *ምንድ ነው እሱ*

- ***መሠረት፡- / ተዋሀዶ ተቀምጣበት ወደነበረው ወንበር ሔዳ/*** ሁሉም ጥለዋት ሔዶ ***/በጣም ታዝናለች/***

- ፍፁም፡- በጣም ይገርማል ግን ምን ዋጋ አለው ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ እውነትን በመያዛቸውና እውነትን በመናገራቸው ብቻ የመዘመርና የማስተማር ዕድልና መድረክ እየተነፈጋቸው ያሉ ለዚች ቤ/ክ ብዙ ነገር መስራት እየቻሉ መሥራት እንዳይችሉ የተደረጉትን ቤት ይቁጠራቸው የተሃድሶ እንቅስቃሴ አይኑን አፍጦ ወደ ሁላችንም ጓዳ እንደገባ እየተመለከትን ዛሬም አመለካከታችንን ያልቀየርን ብዙዎች ነን የሚያስተምሩንንና የሚዘሙሩልንን መምህራንንና ዘማሪያንን መለየት ይኖርብናል

- ***መሠረት፡-*** አዎን ፍጼ ሕዝበ ክርስትያኑ በዚህ ጉዳይ ተጠያቂ ነው እውነተኛውን የቤ/ክ ትምህርት ለመማር የሚጥርና በትክክል እግዚአብሔርን የሚፈልግ ምዕመን እንደጠፋ አውቃለው ስለ እግዚአብሔር ለመናገር ድፍረት የሚያጡ ስለ ጥቂት ግለሰቦች ሲሆን ግን ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ ብዙ ክርስትያኖች ዛሬም ድረስ አሉ

- **ፍፁም፡-** ይሔ ደግሞ የትም የማያደርስ ከንቱ የድካም ሩጫ ነው የዘመኑን ድብቅ የታህድሶ እንቅስቃሴ ከተዋሕዶ እምነታችን ከስር መሰረቱ በጣጥሶ ለመጣል አገልጋዩም ተገልጋዩም እንደ አንድ ልብ ሃሳቢ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን ሕገ እግዚአብሔርና ስርዓተ ቤ/ክ ይጠበቅ ልንል ይገባል፡፡

- ***መሠረት፡-*** *አዎን ልክ ብለሃልከነበረኝ መንፈሳዊ ሕይወት አንድ እርምጃ ለማደግ ከአሁን በኋላ ከውጪ ሳይሆን ውስጥ ገብቼ እኔም ማድረግ የሚገባኝ ላደርግ ሆስኛለው በዚህ ጉዳይ እንድትረዳኝ ፈልጋለው ፍዔ*

- **ፍፁም፡-** እኔ አላምንም መሲ ሰ/ት/ቤት ገብተሽ ልታገለግይ ነው

- ***መሠረት፡-*** *አዎን ውጪ ሆኜ ብዙ ስራዎችን ማከናውን እንደማልችል እና እውነተኛ አገልጋይ ጠፋ እያሉ ከመናገር በሻገር እውነተኛ አገልጋይ ሆኖ መገኘት እንዳለብኝ አስባለው ከዚህ በኋላ እኔም ውስጥ ሆኜ የድርሻዬን መወጣት ይኖርብኛል እስከ ዛሬ ስትለምነኝ እንቢ ብዬክ ነበር አሁን ግን ፍቃደኛ ሆኛለው*

- ፍፁም፡- በጣም ደስ ይላል ዋናው ያንቺ ፈቃደኛ መሆንሽ ነው ሌላው ቀላል ነው ለእኔው ተይው እኔ እጨርሰዋለው አሁን ነጠላ አድርጊና ሔደን አንዳንድ ጉዳዮችን እንፈፅም

- ***መሠረት፡-*** እሺ */ወደ ውስጥ ትገባለች/*

- **ፍፁም፡-** ለካስ እላዩ ኬክ ውስጡ ፌክ የሆነ ሕይወትን ይዘን ነው እስከዚች ሠዓት የደረስነው አሁንስ አይበቃንም አይ አንቺ ተዋሕዶ ስንቱን ጉድ በጉያሽ ተሸከምሽ */ መሠረት ነጠላ ለብሳ ትገባለች/*

- **ተዋሕዶ፡-** */ አዝና ና ተክዛ ጥቁር ልብስ ለብሳ ትገባለች/* የወለድኳቸው ልጆቼ እነዚህ ብቻ ይሆኑ? የአህዛብ ማላገጫ የመናፍቃን መተረቻ ስሆን ከጎኔ የሚቆም ስለኔ የሚመሰክርልኝ ማን ይሆን? ሁሉም ከሩቅ ሆኖ ከተከተለኝ ቀርቦ የሚያጽናናኝ አለውልሽ የሚለኝ ማን ማነው? መቼ ይሆን ከቤቴ ውስጥ ቀስት እና ጦርነት የሚሻረው? መቼ ይሆን እውነተኛ አገልጋይ የማገኘው? ማንስ ይሆን ይሔን በላዬ ላይ የተደረበብኝን የሃዘን፣ የመከራና የሰቆቃ ልብስስ የሚያወልቅልኝ */ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች/*

- ***/ ፍጹምና መሰረት ተዋሕዶ የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ወጥተው ይሔዳሉ ከውስጥ ተዋህዶ የሚለው ዝማሬ እስከመጨረሻው ይዘመራል።***

- *ተዋሕዶ ተዋሕዶ ሠማያዊ*
- *የፀናች የፀናች ሃሌሉያ*
- *ተዋሕዶ ተዋሕዶ መንፈሳዊ*
- *የመንፈስ መብራትህ የመንፈስ መብራትህ ሃሌሉያ*
- *ተዋሕዶ ተዋሕዶ መለኮት*
- *ንፅህት እምነትህ ንፅህት እምነትህ ሃሌሉያ*

❖ ባንቺ ቢያምኑ ባንቺ ቢያምኑ ቅዱሳን

❖ ድል ነሱ ሰይጣንን ድል ነሱ ሰይጣንን ሃሌሉያ

❖ ባንቺ ቢያምኑ ባንቺ ቢያምኑ ሰማዕታት

❖ ተፈተኑ በእሳት ተፈተኑ በእሳት ሃሌሉያ

❖ እንደወርቅ እንደወርቅ ተፈትነው

❖ አበራ ገድላቸው አበራ ገድላቸው ሃሌሉያ

❖ እንኑር እንኑር በእምነታችን

❖ በተዋሕዶ መክበሪያችን በተዋሕዶ መክበሪያችን ሃሌ ሉያ

**ተዋሕዶ፡-/ ወጥታ ትሔዳለች መብራት ይጠፋል መጋረጃ ይዘጋል።/**

# ተ …ፈ ፀ… መ

**❖ ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን!**

❖ ሚያዝያ 2003 ዓ/ም

ድርሰት፡-

ለዩፌ፡ገብርኤል